# KDE ፖሊሲ- የአደጋ ቁጥጥር

ለድንገተኛ ሁኔታዎች እና አደጋዎች ቀድሞ መዘጋጀት ለተማሪዎች፣ ለሠራተኞች፣ እና ትምህርት ቤቱን ለሚጎበኙ ሰዎች ደሕንነታቸውን ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሲሆን ደሕንነትን በተመለከተ ለመከላከል የሚቆም መሆን አለበት። በተጨማሪ ለሁሉም ለሚመለከታቸው አካላት የአደጋ ዝግጁነት ዕቅድ እንዳለ እና ተማሪዎች እና ሠራተኞች ለዚህ አስፈልጊውን የመከላከል ስልጠና እንደወሰዱ እንዲያውቁት ማድረግ ሞራላቸውን ያጠናክራል። መከላከል፣ ዝግጁነት፣ ምላሽ መስጠት እና ማገገሚያ በየድንገተኛ አደጋ ምላሽ መስጫ እና የአደጋ ቁጥጥር DPS Emergency Response and Crisis Management (ERCM) የተቀመጡ የአደጋ ቁጥጥር ሂደቶች ናቸው።

የሥራ ቦታ አስተዳዳሪዎች፣ ወይም ወኪሎቻቸው፣ ትምህርት ቤቶቻቸው የሚከተሉትን መስፈርቶች በማሟላት የ DPS ERCM መርሃ ግብርን ተፈጻሚ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፥

የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የአደጋ ጊዜ ምላሽ ሰጭ ቡድን (E-Team) በዲስትሪክቱ የሚሰጠውን የ ERCM ስልጠና በየዓመቱ መካፈል ይኖርበታል።

- የሥራ ቦታ አስተዳዳሪው፣ ወይም ወኪሉ በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ በ ERCM ዕቅድ መሰረት የድንገተኛ አደጋ ቁጥጥር ዕቅድ በየዓመቱ ያቀርባል።

- የትምህርት ቤት የአደጋ ጊዜ ምላሽ ሰጪ ቡድኖች ሁሉንም የትምህርት ቤት ሠራተኞች (ተማሪዎችን፣ ፋሲሊቲ እና የምግብ አገልግሎት ሠራተኞችን ጨምሮ) ተገቢውን የ ERCM አፈጻጸም በተመለከተ ስልጠና ይሰጣሉ።

- የሥራ ቦታ አስተዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው ትምህርት ቤቶቻቸው በየወሩ እሳት ቢነሳ ስለሚወሰድ እርምጃ ልምምድ መደረጉን ማረጋገጥ አለባቸው።

- የሥራ ቦታ አስተዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው ትምህርት ቤቶቻቸው በ ERCM መርሃ ግብር በሚታዘዘው መሰረት በሁሉም ዓይነት ልምምዶች ላይ መሳተፋቸውን ያረጋግጣሉ።

የሥራ ቦታ አስተዳዳሪዎች እና የትምህርት ቤት ሠራተኞች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለሚወሰዱ የአደጋ ጊዜ ምላሾች አፈጻጸም ያሳውቃሉ።

የዲስትሪክቱ ERCM መርሃ ግብር ከብሔራዊ የአደጋ ቁጥጥር ስርዓት National Incident Management System (NIMS) የተጣጣመ ይሆናል።

ከላይ የተቀመጡትን የሥራ ኃላፊነቶች በመወጣት ላይ፣ ሁሉም የ DPS ሠራተኞች በኮሎራዶ ስቴት የተሻሻሉት 22-32-109.1 (4) እና C.R.S. ደንቦች ይገዛሉ። 22-32-109 (4)

እንዲጣጣም ተደርጎ የተዘጋጀ፥ ኦክቶበር 19፣ 2000
እንደገና የተሻሻለው፥ ጃንዋሪ 17፣ 2008

ሕጋዊ ዋቢዎች፥ C.R.S. 22-32-109.1 (4)